# የምትሃት ትርዒት

ተሻለ መንግሥቱ

አንድ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማር ተማሪ ለአባቱ ‹አባዬ፣ በት/ቤታችን ነገ የሚቀርበውን የምትሃት ትርዒት ለማየት ሦስት ብር ክፈሉ ተብለናልና ስጠኝ› ይለዋል፡፡ አባትም ‹አዬ ልጅነት፣ እኔ አባትህ በአምስት መቶ ብር ደመወዝ ይህን ሁሉ ቤተሰብ ወር እስከ ወር ቀጥ አድርጌ መያዜ ራሱ ምትሃት አይደለም? ታዲያን እዚሁ እቤትህ እኔ አባትህ ምትሃት እያሳየሁህ የምን ገንዘብ ከፍሎ ማየት ነው?› ይለውና ለምትሃት ቀርቶ ለዳቦም የሚሆን ሣንቲም ለማግኘት መቸገሩን ያረዳዋል ፤ ማስረዳት ጥንት ያኔ በደጉ ዘመን በመቅረቱ፡፡ ዛሬ ዛሬ ማርዳት እንጂ ማስረዳት የለም፡፡

የሀገራችን ኑሮ ጦፏል፡፡ ከቃላት የመግለጽ አቅም በላይ ተቃጥሏል፡፡ በዚያም ምክንያት ብዙው ዜጋ የሚያደርው ጠፍቶት እንዲሁ ፈዝዟል፡፡ ይህን ያህል ምን እንዳነሆለለን አይገባኝም፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ በምትሃት የሚተዳደረው ሰው እጅግ ብዙ ነው፡፡ የደመወዙን መጠን የምናውቀው ሰው - ከሦስት ቀናት ያልበለጠ ሊያኖረው እንደማይችል የምንረዳው ብዙ ደመወዝተኛ - በማይገባን ምሥጢር በየቀኑ መጠጥ አፉ ላይ ለግጦ እናየዋለን፤ የ120 ብር ኪሎ ሥጋ ከባልንጀሮቹ ጋር ሲቀረጥፍም  እናስተውላለን፡፡ የተሻለ ደመወዝ አለን የምንል ደግሞ ከቤታችን ሥጋና ቅቤ ከጠፉ ዓመታት ተቆጠሩ - በተለይ ከ97 ምርጫ በኋላ፡፡ ውጪ ማምሸትም ከብርቅነት ተቆጠረ - የቤት ሽሮ ሳይሟላ እንዴት ተደርጎ ውጪ ይመሻል? የወጉን ለማድረስና የሃሳብን ትርምስምስ ከወዳጅና ጓደኛ ጋር ተካፍሎ አእምሮን ፈታ ለማድረግ ከውስኪና ቢራ የሚወርዱ የወራጅ ቀጣና አባላት በየሀበሻ አረቂ ቤቱ ሲያውካኩ ያመሻሉ - እናመሻለን፤ ሌላ ምን ምርጫ አለን? አለበለዚያ በሃሳብና ጭንቀት ድርና ማግ ተተብትበን መውጫ በማጣት ልናብድ እንችላለን፡፡ የዚህ ዓይነቱ የተመሰቃቀለ ሕይወት መነሻው ምሥጢር ሆኖብናል፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ሕይወት ፈርጀ ብዙ ናት - እንደማንኛውም ከተማ ሁሉ፡፡ የኑሮ ልዩነቱ ግን ከየትኛውም ሀገር የሚብስ እንጂ የሚስተካከል እንኳን አይደለም፡፡ አንድ ሰው በአንድ ቀን አዳር እንዴት አንቱ የተባለ ቱጃር ወይም ሙልጭ የወጣ ድሃ እንደሚሆን ዕንቆቅልሽ ነው - የማይገባ፡፡ ከተማዋ ውላ የምታድረው በፈጣሪ ጥበብና ጥበቃ እንጂ አስተዳዳሪ ያላት አትመስልም፡፡ ጉልበተኛ ከሆንክ ሁሉም ነገር አለህ፡፡ ፈሪሃ እግዚአብሔርና ጤናማ ኅሊና ካለህ ከእግዚአብሔርና ከጤናማ ኅሊና በስተቀር ምንም የለህም፡፡ እነዚህ ደግሞ በንጹሕ ኅሊና እንድትደሰት ያደርጉህ ይሆናል እንጂ ለቁሣዊ ሕይወትህ ደንታ ያላቸው አይመስሉም፡፡ እናም ነፍስህ በንጽሕናዋ ልትደሰት ብትችልም በተወሰነ መልኩ ሥጋህ ሊከፋብህና በፈተናም ልትከበብ ትችላለህ፡፡ ያኔ ፈጣሪና ንጹሕ ኅሊና ሊከዱህ ዳር ዳር ይላሉ፡፡ በሠፊው መንገድ ልታመራ ከቆረጥህ ሰው የመሆንህን አንጡራ ሀብት ትቀማና የሁሉም ቁሣዊ ሀብቶች ባለቤት የምትሆንበትን ዘዴና ብልኃት ከቢጤዎችህ ትማራለህ፡፡ ከዚያ አዲስ አበባን በቀንና በሌሊት በሽንጣም ዘመናዊ አውቶሞቢል እየተሽከረከርህ መምነሽነሽ ነው፡፡ ነገ ለራሱ ይጨነቅበታል - አንተ ለምንም መጨነቅ ሣይኖርብህ በሚሊዮኖች ወገኖችህ ደምና ወዝ መደሰት ብቻ ነው የሚጠበቅብህ፡፡ ነጋዴም ሁን፣ ፖለቲከኛም ሁን፤ ተቀጣሪ ሠራተኛም ሁን፣ ዋናው ኅሊናህን እቤትህ አስቀምጠህ ሆድህ ያዘዘህን መፈጸም ነው፡፡ ለዚያ ደግሞ እንደግብአት ዘውገኝነትና ጠባብ ብሔርተኝነት ዋስ ጠበቃ እንደሚሆኑህ ዐውቀህ እስከጥግ ልትጠቀምባቸው ይገባሃል፡፡ በሌላ በኩል ሰፋ ያለ የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ እንዳይኖርህ መጠንቀቅ አለብህ - ይሄ ዓይነቱ አስተሳሰብ ለዕድገትህ ፀር ነው፡፡ በሀብት ሽቅብ ለመስፈንጠር የኢትዮጵያን ስም በፍቅርና በቅንነት ካነሳህ ወዮልህ! ‹በማን ላይ ቆመሽ ወያኔን ታሚያለሽ› የሚለውን አዲስ ተረትና ምሣሌ ማጤን ይጠበቅብሃል፡፡ የምትከብረው በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ወጪና ኪሣራ መሆኑን ካልተረዳህ ሁሉንም የምትቀማበት ዘመን እንደሚመጣ ዕወቅ - በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የምትከብረው ከአስብቶ አራጆች ጋር ተስማምተህና ተሞዳሙደህ እስከቀጠልህ እንጂ ጉዳይህ ሲሞላ ሽርተት የምትል ከሆንክ ተዘጋጅተው ከሚጠብቁህ የማጥቂያ ካርዶች ባንደኛው ዘብጥያ ትወርዳለህ፤ የቁሣዊ ዕድገትህ ምንጭ የወያኔ ችሮታ የታከለበት ያንተው ኅሊናቢስነት  እንጂ የብቃት ደረጃህ ከፍተኛነት እንዳልሆነ ካልተረዳህ ተጎጂ ነህ፡፡ በብፅዕና መከበር የለም - በዚህ ዘመን የሚከበረው ራስን ከድቶ ኅሊናን ለባዕድ አስተሳሰብ ካስገዙ ብቻ ነው፡፡ ይህ ውርደታዊ ዕድገት ጥንትም ነበር፤ አሁንም አለ፡፡

ትናንት አለቤሾው ላይ አዘጋጁ አለባቸው ተካ በፕሮግራም መግቢያነት ይጠቀምባት የነበረችውን  ኩሽና እምትመስል ጢስ የጠገበች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ በኪራይ ሲኖር የነበረ ሰው ዛሬ የመዋኛ ገንዳና ጃኩዚን የተባሉ የቅንጦተኛ ኑሮ መገለጫዎች የተሟሉለት የተንጣለለ አውሮፓዊ ግቢ ውስጥ አኗኗሩን እንኳን በቅጡ ሳያውቅበት  ትናንትናና ከትናንት በስቲያ ድሃ ከነበረ ቤተሰቡ ጋር ሲኖር ብታይ መቅናት የለብህም፡፡ አንተም እርሱን የመሆንና ያለመሆን መብት ስላለህ በምንም ነገር ልትቀና አይገባህም፡፡ ኑሮ በአዲስ አበባ ዕንቆቅልሽ መሆኑን ተገንዝበህ ነፍስህን አውለህ ለማሳደር መታገል ወይም ‹ጅብ ከሚበልህ በልተኸው ተቀደስ › በሚለው የሆድ አደር መመርያ መሠረት የነበረህን ዓላማ - ከነበረህ-  ቀይረህ ወደሀብቱ ተራራ መጓዝ ነው፡፡ አትጠራጠር - ይሳካልሃል፡፡ ግን ጸሎትህንና እምነትህን ካልለወጥህ አይሆንልህም፡፡ በነጻ እሚገኝ ነገር የለም፡፡…

ጸሎትህ ባጭሩ ይህን ይምሰል፡- ‹ አቤቱ ወያኔ ሆይ በጠበንጃ ጫፍ የምትኖር ደደቢታዊ መንፈስህ ትባርከኝ፡፡ ስምህ በዲያቢሎስ መንግሥት ገናና እንደሆነ ሁሉ በእኔም ቤት እንደዚያው እንዲሆን ፈቃድህ ይሁንልኝ፡፡ ከሀብት ማግኛ ጠላቶቼ ከመድረክና ቅንጅት ብሔራዊ መናፍስት እንዲሁም እነሱ ከሚያቀነቅኑት የኢትዮጵያዊነት አባዜ  በኪነ ልደትህ ወሞሼህ ጠብቀኝ፡፡  ዐይኔ ያየውን መኪና ሳልነዳ፣ የልጆቼን እናት አሮጊት ሚስቴን ፈትቼ ቀልቤ ያረፈባትን ውብ ኮረዳ ሳላገባ፣ ልቤ በተመኘው ምግብና መጠጥ ሁሉ ሳልደሰት፣ ለትውልድ የሚተርፍ ገንዘብ በባንክ ሳላከማች… በጅምር እንዳልሰናከል የዐድዋና የአክሱም ወያኔያዊ አበጋሮች ተለምነውኝ ጸሎቴ በወያኔ/ኢሕአዴግ መንበረ ሣጥናኤል ውኩፈ ለይኩን ይሁንልኝ፡፡ አሜን፡፡ › ጸሎትህ አጠር ይበል - ሲንዛዛ ደግ አይደለም - ያስጠረጥርሃል፤ ያስመነጥርሃልም፡፡

አዲስ አበባ ላይ ኑሮ በዘመናዊ የምፀት አገላለጽ ‹አሸወይና› እንደሆነች አየን፡፡ የኑሮ ዕንቆቅልሹ ከአእምሮ በላይ እንደሆነም በጣም ባጭሩ ተመለከትን፡፡ የዛሬ ሕይወቱን ለነገ ለማሳደር አቅሉን ስቶ የሚራወጥባት አዲስ አበባ በዚያው ልክ ሳይሠራና ሳይለፉ ሕይወት ቀኝ በቀኝ የሆነችለት ዘራፊና ሌባም ብዙ ነው፡፡ ቀን ቀን በከተማዋ የሚርመሰመሱትን መኪኖችና ካለአንዳች ሥራ በሥራ ሰዓቶች በየአደባባዩና በየሥፍራው የሚንቀሳቀሰውን የሰው ብዛት ስታዩ ‹ይህ ሕዝብ ሥራ የሚሠራው መቼ ነው? ሌሊት ሌሊት ይሆን እንዴ?› ብላችሁ ልትጨነቁና ይህ ሁሉ ዜጋ ሥራ የሌለው ይሆን ይሆናል ብላችሁ የምትገምቱ ከሆነ ደግሞ ‹ታዲያ ማንስ ነው ሠርቶ የሚያኖረው?›  ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ አስጨናቂ ሀገራዊ ምስል ተደቅኖብናል፡፡ እንዴት ይወገዳል? ወደፊት የምናየው ይሆናል፡፡ ነገሩ ግን የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የኑሮ ውድነቱ ብቻ አንድ ቀን የሚፈነዳና ሀገሪቱን ለከፋ ምስቅልቅል የሚዳርግ ስለመሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ የኑሮ ውድነቱ ከቀን ቀን እየናረ ባለበት ሁኔታ ገንዘብ የሚያጋብሱት ዜጎች ደግሞ ከአጠቃላዩ ሕዝብ ሲነጻጸሩ እጅግ ኢምንት የመሆናቸው ነገር ተደማምሮ ቀውሱን እንደሚያፋጥኑት የታመነ ነው፡፡ የሚገርም ወቅታዊ ሁኔታ!!

የመኪናውን ነገር ስናነሳ መርሳት የሌለብን ነገር አለ፡፡ በቻይና ዋና ከተማ አምስት ሚሊዮን የሚጠጉ መኪኖች ሲርመሰመሱ በአዲስ አበባ ከሁለት መቶ ሺህ የሚያንሱ እንደሆነ እንሰማለን፡፡ ያበዛቸው ታዲያ ምኑ ነው? ብለን ስንጠይቅ መልሱ የመኪና መንገዱ ጥበት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ አንድ ሺህ ለሚደርሱ መኪኖች የተሠሩ መንገዶች ለዚህ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲወዳደር ኢምንት ለሆነ የመኪና ቁጥር ሊበቁ አልቻሉም፡፡ በዳዴ በምትሄድ ሀገር መቶ ሺና ሁለት መቶ ሺ መኪኖች ብዙ ናቸው፡፡ አሁን አሁን ሰውና መኪና እየተጋፉ መሄድ ጀምሯል፡፡ ያደጉ አገሮች አራትና አምስት ንብርብር መንገዶች ሲሠሩና ዕድገታቸውን ጠብቀው ሲተሙ ከአፍ እስከ አፍንጫቸው አርቀው የማያስቡት የኛ መንግሥታት እንደኤሊ በሚንተት የዕድገት ትልማቸው ሰውና መኪናን የሚለይ መንገድ ሊሠሩ አልቻሉም፤ ሠሩን ቢሉም የተሠራውና የሚሠራው ከዕድገቱ ጋር ሊመጣጠን አልቻለም - በየቀኑ በብዙ መቶዎች ምናልባትም በሺዎች ለሚገባ መኪና የሚሠራው መንገድ ግን በተለይ አሁን አሁን የተቦረቦረን አስፋልት ከመለጠፍና የመንገድ ደሴቶችን ከማስዋብ የዘለለ አይደለም፡፡ በዚሁ ያልተመጣጠነ ሙከራቸው ሲኮፈሱና ሲመጻደቁ ማየት ደግሞ እጅግ ያሳዝናል፡፡ ሠርቶ ችግርን ካስወገዱ በኋላ መኩራራት የተገባ ነበር፡፡ ግን ለአፍዝ አደንግዝ የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል በሚዲያ ጆሮን እየደጋገሙ መጠለዝ አግባብ አይደለም፡፡ አሥራ አምስት ደቂቃ ለማይፈጅ መንገድ ከአንድ ሰዓት በላይ እየፈጀን ሥራ የሚረፍድብንና ከአለቆቻችን የቃል ግሣጼና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚደርስብን ዜጎች ይህ የመንገዶች መስፋፋት ዜና ለኛ ቀልድ ነው፡፡ አልተሠራም ማለት ግን አይደለም - ችግሩን ሊቀርፍ በሚችል ሁኔታ አልተሠራም ነው የምንለው፡፡ በየቦታው ማነቆ ነው፡፡ ማስተንፈሻዎች በበቂ አልተሠሩም፡፡ ከአሁን በኋላም ወደላይና ወደታች ካልሆነ በስተቀር የጎንዮሽ የመንገድ ሥራ አያዛልቅም፤ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና፡፡ ትርፉ ቤት ማፍረስ ብቻ ነው፡፡ እስከመቼስ እያፈረሱ መቀጠል ይቻላል? ብሎ ብሎ ሁሉም እኮ ሊፈርስ ነው፡፡

የመንገዱ ጉዳይ እዮዬም ሲዳላ ዓይነት ነው፡፡ አሁን ማንቁርታችንን ይዞን ያለው የኑሮ ውድነቱ ነው፡፡ በነጋሪት ጋዜጣ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በግልጽ ባልታወጀ ጦርነት እያለቅን ነን፡፡ እየኖሩ ያሉት ጥቂቶች ናቸው፡፡ ብዙዎቻችን ሞትን በሚያስመኝ ሁኔታ በኑሮው እያለቀስን እንገኛለን፡፡ ብዙ የምግብ ዓይነቶች ከመወደዳቸው የተነሣ ከብዙዎቻችን የቀድሞ ደህና ኗሪዎች የምግብ ዝርዝር ተሠርዘዋል፡፡ ለምሣሌ ቅቤና ሥጋ ጥርኙ ብርኙ ሲሉ ቆይተው ለይቶላቸው ከኔ ቤት ከተሰናበቱ ሦስት ወራት ተቆጠሩ - ብርቱካንንም፣ ወተትንም፣ ሙዝንና ሌሎቹንም ጠቃሚ የምግብ ይዘቶች አስከትለው፡፡ ይህ የኔ ችግር የቅንጦት ነው፡፡ በሌሎች ቤቶች ደግሞ ኪሎው ከአሥራ አምስት ብር በላይ የሚሸጠው ሽምብራ ጠፍቶ ለከፋ ርሀብ የተጋለጡ እንዳሉ ዐውቃለሁ፡፡ ርሀብ ደግሞ ጊዜ አይሰጥም፡፡ መሪዎችን በሀገራችን ርሀብ የለም ይበሉ እንጂ ሁላችንም ርሀብተኞች ነን፡፡ ርሀብ ደግሞ ፍቺው እንደዬሀገሩ ይለያያል፡፡ ነፍስ ውሎ ስላደረ ብቻ አንድ ሰው አልተራበም አይባልም፡፡ እኔ ራሴ የርሀብ ተጠቂ መሆኔን ማስረዳት እችላለሁ፡፡ አንድ በሠለጠነው ዓለም የሚገኝ የማይራብ ዜጋ በቀን የሚያገኘውን የምግብ ራሽን አገኛለሁ ወይ? ብዬ ራሴን ስጠይቅ የማገኘው መልስ ‹ተኼ፣ ለምን ትቀልዳለህ? የምን መቀናጣት ነው? በብረት የከበረ የጥቁር ጤፍ እንጀራ ከዶኬ ወጥህ ጋር ካገኘህ የምን ፕሪሞ ሴኮንዶና ቴርዞ፣ የምን ሥጋ፣ወተት፣ዕንቁላል፣ዓሣ፣ፓስታሹታ፣ቪልኮተሌት፣ስካሎፕ፣አኜሎዲቢቴሎ፣ፓይ፣ቤከን፣ቋሊማ፣ ስቴክ፣ ሙዝ፣ቴላቴሊ፣ሞርታዴላ፣ላዛኛ፣ሩዝ፣ብርቱካን፣ማንጎ፣ፓፓያ፣ሙዝ፣ፖም፣ለውዝ፣ዙኪኒ፣ሾርባ፣...(የስንቱን ወስፋት አላውሼው ይሆን - ይቅርታ፤ ብቻ የምግብ ሰዓት አይሁን) ... ጌታው ተው እንጂ...› የሚል ነው፡፡ አዎ፣ ከዚህ አንጻር ከተመለከትነው የርሀብተኛውን ቁጥር፣ ቁጥር አይገልጸውም፡፡ 99 በመቶ የምንሆነው ዜጎች የኗሪ አኗኗሪ ስለመሆናችን የሚነገርልን እንግዲህ ከዚህ መሠረታዊ ጭብጥ በመነሳት ነው፡፡ እናስ የኔ ርሀብተኝነት ተገለጠላችሁ ይሆን አሁን? እንጂ መኖር ከተባለማ ዐይናቸው ሳያይ ዕጃቸው የገባላቸውን የገዳም አካባቢ ቅጠል እየሸመጠጡ በቀን አንዴ የሚቀምሱት የበቁ አባቶችስ ይኖሩ የለምን? የነሱ በምርጫ - የኛ መንግሥታችንና መንግሥታዊ ዕጣችን በጣሉብን ግዴታ መሆኑ ነው ልዩነቱ፡፡ እናም በአሸር ባሸር ምግብ ሆድን ቆዝሮ ዐይቶ የዋጠ እባብ መስሎ መንቀሳቀስ በቅጡ መኖርን እንደማያመለክት መገንዘብ ያሻል፡፡ ለነገሩ ይሄም ከጠፋ ሰነባበተን፡፡ የአሁኑ ብሶ ቁጭ አለ፡፡

የኑሮ ውድነት ከተነሣ ዘንድ የሚከተሉትን የግንባታ ዕቃዎች የወቅቱን ዋጋ ከአሥር ዓመት በፊት ከነበራቸው ዋጋ ጋር እያነጻጸርኩ ልግለጽላችሁ፤ በዚያውም በአሁኑ ወቅት የደረስንበትን የብር የመግዛት አቅም ግሽበትና ቤት የሚሠራው ማን ሊሆን እንደሚችል ትረዳላችሁ፡፡ በልተውት አንጀት ጠብ የማይል አንድ ተራ የፍስግ ምሣ በአማካይ ብር 35 በሆነበት ዘመን፣ የተሸቀበ አንድ ኪሎ ጥብስ ወይ ጥሬ ሥጋ በአማካይ 100 ብር በሆነበት ዘመን፣ ጭብጥ ባቄላ ገዝቶ አፍን ለመሻር ከበቆልት አዟሪዎች ከአምስት ብር በላይ መክፈል በሚያስፈልግበት ዘመን፣ ሻይና ቡና ጠጥተህ በደጉ ዘመን ለቁርጥና ለውስኪ ከምታወጣው ገንዘብ የበለጠ በምትጠየቅበት ወቅት፣ ሥጋ መግዛት ይቅርና በሉካንዳ በር ካለፍክ ሥጋን ለማየት ገንዘብ የምትከፍልበት ጠማማ ዘመን በግምባር እየመጣ ባለበት አስቸጋሪ ወቅት፣... ላይ እንገኛለን፡፡ ይህን ጉድ ዘመን ለልጆቻችን እናወርሳለን ወይንስ የተሻለ አማራጭ ይኖረናል? እናስብበት፡፡

| ተ.ቁ | የዕቃው ስም | መለኪያ | የአሁን ዋጋ(በችርቻሮ) | በ90ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስሚንቶ | ኩንታል | 350 ብር | 50 ብር |
| 2 | አሸዋ | ባለ16ሜ.ኩ | 6000 ብር | 1500 ብር |
| 3 | ጠጠር | ›› | 5600 ብር | 1400 ብር |
| 4 | ሽቦ | በኪሎ | 30 ብር | 30 ብር |
| 5 | ባለ8 ፌሮ | ቤርጋ | 123 ብር | 18 ብር |
| 6 | ባለ10 ›› | ›› | 195 ብር | 28 ብር |
| 7 | ባለ 12 ›› | ›› | 275 ብር | 31 ብር |
| 8 | ባለ14 ›› | ›› | 368 ብር | 41 ብር |
| 9 | ባለ16 | ›› | 478 | 50 ብር |
| 10 | ምሥማር | ኪሎ | 30 ብር | 8 ብር |
| 11 | የቆርቆሮ ምሥማር | ኪሎ | 45 | 10 ብር |
| 11 | አናፂ/ግምበኛ | የ ቀን ውሎ | ከ120 ብር በላይ | (ለማጁን) ከ15 ብር እስከ 30 ብር |
| 12 | ረዳት ወዛደር | ›› | ከ50 ብር በላይ | ከ5 ጀምሮ እስከ 15 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 13 | ቆርቆሮ | 32ጌጅ | ከ160ብር በላይ | 38ብር |
| 14 | የውኃ ቀለም | ጋሎን | 140 ብር | 50 ብር |

**ልዩ ማስታወሻ፡**- በኢትዮጵያ ከመኖር በለየለት ሲዖል ውስጥ መኖር ይሻላል፡፡ ይህን ወረቀት ጽፌ ከጨረስኩ በኋላ ለመላክ ስሞክር ኢንተርኔት አይሠራም፤ ደጋግሜ ሞከርኩ አሁንም አይሠራም፡፡ መስመሩ ይገባል ነገር ግን ግንኙነት እንዳይኖር በቅጥረኞች ድረገፅ አምካኞቹ የቻይና ‹ዐይጦች› ታግዶኣል፡፡ በዚህች እንኳን እንዳንተነፍስ ያለብንን እመቃ ተመልከቱ፡፡ እንዲህ የሚሆነው ደግሞ ዛሬ ብቻ ሣይሆን ሁልጊዜ ነው፡፡ ከሌላው ሁሉ ይሄኛው ድርጊታቸው ይበልጥ ያሣርራል፡፡ ሳይሞቱ መከፈንን የመሰለ መጥፎ ነገር የለም፡፡ ርሃብን በሆነ ነገር ማስታገስ ይቻል ይሆናል፤ ይህ ዓይነቱ የኅሊና ነጻነት ርሃብ ግን እጅግ ሲበዛ መሪር ነው፡፡ ሞትን ያስመርጣል፡፡